# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 59 ሰኔ 25 ቀን 2001 ዓ.ም


ተፈጥሮአዊ ልዩነቶች አሉን፣ ቢሆንም፣ በላቀና ለነፃነት በተከፈለ መስዋእትነት የተፈተለ፣ የተጋመደና የተሸረበ፣ የአንድነት ታሪክ ባለፀጋዎችም ጭምር ነን ። ስለሆነም፣ ስለ ህብረት ትግል ስናሰላስል፣ የዛሬውን የቋንቋና የስነ ልቡና ልዩነቶች መኖር፣ እንደ ጋሬጣ ሳይሆን፣ የዚህችን ታሪካዊት ሃገር ቀጣይነት እንደሚያጠብቅ የማሪያም መቀነት ልናየው ይገባል እላለሁ ። የህብረት ትግል አንዱ ዋነኛ ምክንያት ይህ ልዩነትና አንድነት የሚያስገድደው የፖለቲካ ዘይቤ ይመስለኛል ።

ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ

## የወያኔ የፍርድ ቤት ድራማ በእነ ብርጋዲየር ጀኔራል ተፈራ ማሞ ላይ የሀሰት ምስክሮችን ማሰማት ጀመረ

ወያኔ በለመደው የፍርድ ቤት ድራማ በእነ ብርጋዲየር ጀኔራል ተፈራ ማሞ ላይ የሀሰት ምስክሮችን ማሰማት ጀመረ። ምስክሮቹ በሀሰት ከመመስከር እንዲቆጠቡም ማስጠንቀቂያ ተሰጠ።

ወያኔ ባለፈው ሰኞ ሰኔ 23 ቀን 2001 ዓ.ም በፈጠራ ክስ በከሰሳቸው በእነ ጀነራል ተፈራ ማሞ ላይ የሀሰት ምስክሮችን ሲያሰማ መዋሉን ዘጋቢያችን ከአዲስ አበባ የገለጸልን ሲሆን፣ በምስክርነት ከቀረቡት መካከል አብዛኞቹ የወያኔ ሰላዮች እንደሆኑ ለማወቅ ተችሏል። ምስክር ተብየዎቹ አስቀድመው እንዲያጠኑት የተደረገውን ቃል በትክክል መናገር አቅቷቸው ሲደናበሩና የሚናገሩት ጠፍቷቸው ቁልጭ ቁልጭ ሲሉ እንደነበር ዘጋቢያችን ገልጿ፣ በምስክርነት የመጡት ሰዎች በሙሉ ወታደራዊ መኮንኖቹ ከተከሰሱበት ጋር በተያያዘ ምንም እውቀት የሌላቸው እንደነበር ጠቅሷል። ስለጦር መሳሪያ የማያውቁ ሰዎች፣ ስለ መሳሪያ አይነት እንዲናገሩ፣ ስለወታደራዊ እቅድና አመራር የማያውቁ ሲቪሎች ደግሞ ስለ መፈንቅለ መንግስትና ስለ ወታደራዊ አደረጃጀት መናገራቸውን የጦቀመው ዘጋቢያችን ፣ የወያኔው አቃቢ ህግ በፊት በቅንጅት እስረኞች ላይ ሲፈጽም የነበረውን አይነት ድራማ በእነ ብ/ር ጀኔራል ተፈራ ማሞ ላይ ሲሰራው መመልከቱን ተናግሯል።

ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## ታዋቂ ኢትዮጵያውያን አገር ጥለው በመውጣት ላይ ናቸው

እውቁ የሰብአዊ መብት ተሟጋች ጠበቃ አበበ ወርቁ ከአገር መውጣታቸው ታወቀ። ከ1960ዎቹ የተማሪዎች የፖለቲካ ትግል ጀምሮ በኢትዮጵያ የዲሞክራሲ ለውጥ እንዲመጣ ከፍተኛ ተጋድሎ ሲያደርጉ የቆዩት ታዋቂው የህግ ባለሙያ አበበ ወርቁ፣ የወያኔው አገዛዝ ባደረሰባቸው ተጽእኖ ምክንያት አገር ጥለው መሰደዳቸው ታውቋል።

ጠበቃ አበበ ወርቁ አገር ጥለው ለመሰደድ የተገደዱት ከአዲስ ብሮድካስቲንግ ኩባንያ ጋር በተያያዘ በቀረበባቸው የሀሰት ክስ ሲሆን በቅርቡ ለሳምንታት ታስረው በ130 ሺ ብር ዋስትና መለቀቃቸው መዘገቡ ይታወሳል። የወያኔው አገዛዝ በአዲስ ብሮድካስቲንግ ኩባንያ ላይ የሀሰት ውንጀላ በማቅረብ፣ የኩባንያው ንብረት የሆኑትን የሬዲዮ ማሰራጫ እቃዎች፣ የማተሚያ ማሽኖችና የተለያዩ ንብረቶችን መዝረፉ በተለያዩ የዜና ማሰራጫዎች መሰራጨቱን ተከትሎ፣ ከኩባንያው ጋር ዝምድና አላቸው የተባሉ አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያንንም ክስ ተመስርቶባቸው የወያኔን የይስሙላ የፍርድ ሂደት በመጠባበቅ ላይ ናቸው።

አቶ አበበ ወርቁ በኢትዮጵያ የሰብአዊ መብቶች ድርጅት ውስጥ በአመራር ሰጪነት በሰሩባቸው አመታት፣ የወያኔን የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ለአለም በማሳወቅ ከፍተኛ ሚና እንደነበራቸው የሚታወቅ ሲሆን፣ ወያኔም እርሳቸውን ለማጥቃት የተለያዩ ምክንያቶችን ሲፈጥር መቆየቱን ለጉዳዩ ቅርበት ያላቸው ሰዎች ተናግረዋል።

ወደ ገጽ 4 ዞሯል

የዘር መድልዎን ለማጥፋት የሚደረግ ትግል አላስፈላጊ ወደ ሆኑ ጽንፎች እንዳይሄድና አሰቃቂ መዘዞች እንዳያስከትል ከመድልዎው ተጠቃሚ የሆኑ ወገኖች የአገዛዙን ኢፍትሃዊነትና ኢሰብአዊነት ተቃውመው በስማችን ይህ ግፍ ሲፈጸም ዝም ብለን አናይም ማለት ይገባቸዋል:: የደቡብ አፍሪካን አፓርታይድ ለማስወገድ የስርአቱን ግፈኛነት ተቃውመው የታገሉ የነጭ ደቡብ አፍሪካውያን ሚና ምን ያህል ከፍተኛ እንደነበር ልብ ይሏል:: እኛም ከትግራይ ተወላጆች ተመሳሳይ ነገር እንጠብቃለን:: ምክንያቱም ግፍ የሚወልደውን አመፅ መቆጣጠር የማይቻልበት ሁኔታ ላይ ሊደረስ ይችላል: **ርዕሰ አንቀጽ**

ግዜ ግንቦት 7 ዜና

## ወያኔ እድሜውን ለማራዘም ሆን ብሎ የሃይማኖት ግጭቶች እንዲፈጠሩ ከፍተኛ ጥረት እያደረገ ነው

ወያኔ ለዘመናት አብረው የኖሩትን ህዝቦች በዘር ለማጫረስ የዘረጋው ፖሊሲ ሲከሸፍበት በሀይማኖት ሽፋን አዳዲስ ግጭቶችን በመፍጠር የአገዛዙን እድሜ ለማራዘም የሚያደርገው ጥረት ተጋለጠ።

የወያኔው ዘረኛ አገዛዝ፣ ከዚህ ቀደም ህዝቦችን በደማቸውና ባጥንታቸው በመለያየት ለማጫረስ ያደረገው ሙከራ በግንቦት 1997ቱ ምርጫ ሲከሸፍበት፣ ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ ደግሞ ሀይማኖትን ሽፋን አድርጎ ግጭቶችን በማስነሳት ላይ እንደሚገኝ ከትናንት በስቲያ በደሴ እንዲሁም በቅርቡ በጂማ፣ በሀረር፣ በአዲስ አበባና በሌሎችም የአገሪቱ ክፍሎች የታዩት ግጭቶች እንደሚያሳዩ ባለሙያዎች በመናገር ላይ ናቸው።

የወያኔው አገዛዝ ከትናት በስቲያ፣ ማክሰኞ፣ ለዘመናት ተፈቃቅረውና ተከባብረው የኖሩትን የደሴን ክርሲያንና ሙዝሊም ነዋሪዎች ለማጋጨት ያደረገው ሙከራ ከሽፎ፣ ግጭቱ በወያኔ ቅልብ የፌደራል ፖሊሶችና በምእመኑ መካከል መሆኑ የወያኔ ዘረኛ ባለስልጣነት ሲያስደነግጥ የኢትዮጵያን ህዝቦች ግን አኩርቷል።

ጀግኖቹ የደሴና በደሴ ዙሪያ የሚገኙ ነዋሪዎች ለመብታቸው መከበር ያሳዩት ተጋድሎ በአርያነቱ ለሌሎችም ህዝቦች የሚጠቀስ መሆኑን አስተያየት ሰጪዎች በመናገር ላይ ሲሆኑ፣ ወያኔ በህዝቡ ጀግንነት እጅግ በመደናገጡ የፌደራል ፖሊሶችን የጫኑ መኪኖችን በብዛት ወደ አካባቢው መላኩን ምንጮቻችን ገልጸዋል።

የደሴ ከተማ ህዝብ በወያኔ አገዛዝ ላይ የሚያሳየው ተቃውሞ ዘረኛውንና አምባገነኑን መለስ ዜናዊን በማሳሰቡ፣ ያለወትሮው ከተደበቀበት የአራት ኪሎ ምሽግ በመውጣት የአካባቢውን ህዝብ ለማረጋጋት ሞክሮ እንደነበር ያስታወሱት ምንጮች፣ ከአምባገነኑ ጉብኝት በሁዋላ የህዝቡ ልብ ይበልጥ መሸፈቱንም ተናግረዋል። ወያኔም ይህን ህዝባዊ ሀይል መቋቋም ሲያቅተው፣ ክርስቲያኑንና ሙሲሊሙን በማጋጨት የህዝቡን ሀይል ለማዳከም ሴራ መጠንሰሱንና ሴራውም መክሸፉን ምንቶቻችን አክለው አስረድተዋል።

ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## መለስ ስልጣን መልቀቅ የለበትም የሚል ዘመቻ ሊጀመር ነው

በራሱ በመለስ ትዕዛዝ መሰረት "መለስ ዜናዊ ስልጣን መልቀቅ የለበትም" የሚል ሀሳብ በድርጅትና በመንግስት ሚዲያዎች በስፋት እና በዘመቻ መልክ እንዲስተጋባ የኢህአዴግ ፕሮፓጋንዳ ክፍል እቅድ ለማውረድ መወሰኑን የግንቦት 7 ታማኝ ምንጮች ገለፁ::

እንደ ምንጮቹ ዘገባት ወያኔ የሚቆጣጠራቸው የኤሌክትሮኒክም ሆኑ የህትመት ሚዲያዎች በሙሉ፤ በቀጣይ በጉዳዩ ዙሪያ ጥቂት የተመረጡ የወያኔ ካድሬዎችን ቃለ-ምልልስ በማድረግ፤ "መለስ ዜናዊ ሊወርድብን አይገባም" የሚለውን ዲስኩር እንደ ህዝብ አስተያየት የማራገብ ጥቁር ፕሮፓጋንዳ ስራ ላይ -ባተሌ ሆነው ይሰነብታሉ።

ከዚያም በተዳጓኝ በድርጅቱ በኢህአዴግ ውስጥ "መለስ ሊወርድብን አይገባም" የሚል የተቀነባበረ ዘመቻ በመለስ የውስጥ ትዕዛዝ ሰጪነትና በበረከት ፊታውራሪነት መጀመሩን የጠቆሙት ምንጮቻችን፤" ይህ ዓይነቱ የውስጥ ዘመቻ በ አራቱም የተናጠል ድርጅቶች ማለትም በህወሀት፤ በብአዴን፤ በኦህዴድና በደኢህዴግ ውስጥ እንዲጀመር ተወስኗል ብለዋል።

የኮሙኒኬሽን ፅህፈት ቤት ዋነኛ ተላላኪዎች ይህን እቅድ በተገቢው መንገድ የማስፈፀም ሃላፊነት ወስደው "በህዝብ አስተያየት ስም" የተለያዩ ፅሁፎች እየፃፉና እያፃፉ በየሚዲያዎች ማተምና ማሰራጨት መጀመራቸውም ተሰምቷል።

ይህም እየተደረገ ያለው መለስ ለመልቀቅ ቢፈልግም እንኳ ድርጅቱ ኢህአዴግ በጋራም ሆነ እህት ድርጅቶቹ በተናጠል- ስልጣን እንዲለቅቅ አልፈቀዱለትም እንዲባል ነው- መረጃውን ያደረሱን ውስጥ አዋቂ ምንጮች እንደሚሉት።

ጉዳዩን አስመልክቶ መስከረም ላይ የኢህአዴግ ምክር ቤት በሚያደርገው ስብሰባ" ክቡር አቶ መለስ ስልጣን መልቀቅ የለብዎትም፤ በዚህ መስቀለኛ መንገድ ላይ በቆምንበት ጊዜ ያለ እርስዎ ማን ሊመራን ይችላል?" የሚል ሀሳብ በሙግትና በክርክር መልክ እንዲነሳ ይደረጋል ያሉት ምንጮቻችን፤ ምናልባትም ይህ ዓይነቱ የመለስን ቆዳ ለማዋደድ ታስቦ የሚደረገው የይስሙላ ሙግት -ቀጥታ የሚዲያ ስርጭት እንዲያገኝ ይደረጋል ብለን እንገምታለን" ብለዋል።

እነዚሁ ምንጮች እንዳሉት:-"ነባሩን የኢህአዴግን አመራር በአዲስ መቀየር" የሚለው አዲሱ የወያነ ነጠላ ዜማ መለስን ይመለከተዋል ብሎ ማሰብ ሞኝነት ነው ።

ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## የዘረኛነት አገልጋይ በመሆን የሚገኝ ዘለቄታዊ ጥቅም አይኖርም!

የግለሰብ ባህርይ እና ችሎታ የሚወሰነው በዘሩ፣ በብሄሩ፣ በጎሳው ወይም አባል በሆነበት ማኅበር ነው ብሎ የሚያምን አስተሳሰብ «ዘረኝነት» በመባል ይታወቃል፡፡ ዘረኝነት ሰዎችን በቡድን ካልሆነ በስተቀር በግል አያውቃቸውም፡፡ ይህ አገርንና ሕዝብን የሚጎዳ ኋላቀር አስተሳሰብ አንድ ቡድን በሃብትና ሥልጣን የበላይነትን የሚይዝበት አድሎዓዊ ሥርዓት ይዘረጋል፡፡

እ.ኤ.አ 1965 ወጥቶ ከ1969 ጀምሮ በሥራ ላይ የዋለው የተባበሩት መንግሥታት *የሁሉም ዓይነት የዘር-መድሎዎች ማስወገጃ ኮንቬንሽን* «የዘር-መድሎ»ን በሚከተለው አኳኋን ይተረጉመዋል፡፡

የዘር-መድልዎ *«....ዓላማው ወይም ውጤቱ ሰብዓዊ መብቶችንና መሠረታዊ ነፃነቶችን በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚ፣ በማኅበራዊ፣ በባህላዊ ወይም በሌላ ማናቸውም የማኅበራዊ ሕይወት ዘርፍ ውስጥ በእኩል መጠቀምን የሚያጠፋ ወይም የሚያሰናክል በዘር፣ በቀለም፣ በአስተሳሰብ፣ በብሄር ወይም በጎሳ መነሻነት የሚደረግ አድልዖ፣ ማግለል፣ መከልከል ወይም የተለየ አሰራርን መጠቀም ነው፡፡»*

ይህን ትርጓሜ የሚያሟላ የዘር-መድልዎ አገራችን ውስጥ ስለመኖሩ የሚከተሉትን ማስረጃዎች እንጠቅሳለን፡፡

1. የአገሪቱ የመከላከያ ሠራዊትና የስለላ ድርጅት ቁልፍ የአዛዥነት ቦታዎች ሙሉ በሙሉ ማለት በሚያስችል ሁኔታ በትግራይ ዘውጌ ማኅበረሰብ አባላት መያዛቸው ሃቅ ነው፡፡ በፌደራል የመንግሥት መዋቅርና ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ ባላቸው እንደ ቴሌኮሚኒኬሽን፣ የመንገድ ሥራዎች ድርጅት፣ የሲቪል አቪየሽን፣ የኤሌክትሪክና መብራት ኃይል፣ የሕዝብ ማመላለሻ አገልግሎት ባለሥልጣን መ/ቤቶችና ኮርፖሬሽኖች ቁልፍ የኃላፊነት ቦታዎች በአንፃራዊ ስሌት ባብዛኛው በትግራይ ዘውጌ ማኅበረሰብ አባላት ተይዘዋል፡፡ በፌደራል አገዛዝ ውስጥም ዝቅተኛ የክፍል ኃላፊነት የሥራ መደቦች እንኳን ሳይቀር በዘር በመጠቃቀም በርካታ የሃላፊነት ቦታዎች የተያዙት በትግራይ ተወላጆች ነው፡፡ ይህ የፌደራል አገዛዙን የስራ ዘርፎች በትግራይ ተወላጆች የማስያዝ መርሃ ግብር በትግራይ ክልል ቅድመ 1997 ዓ.ም በተደረገ ጥናት በአስር አመት ውስጥ በእዚህ ክልል ሊፈጠር የሚችለውን ከግማሽ ሚሊዮን በላይ የስራ እጥ ቁጥር ለመቀነስ የተዘጋጀው የፖሊሲ ውሳኔ ውጤት ነው፡፡
2. ኢኮኖሚውን በተመለከተም እንደ ኮንስትራክሽን፣ ሪል እስቴት፣ ፋይናንስ፣ ትራንስፖርት፣ የውጭ ንግድና የትራንዚት አገልግሎት የመሳሰሉት በተለይ ዘመናዊ የሆነው ዘርፍ በአብዛኛው በትግራይ ዘውጌ ማኅበረሰብ አባላት የቀጥታና የእጅ አዙር ቁጥጥር ሥር ወድቀዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ወይ የወያኔ አሊያም ከትግራይ ዘውጌ ቡድን ያልሆኑ ኢትዮጵያውያን በአገሪቱ ኢኮኖሚ ውስጥ የመሳተፍ ነፃነታቸው በእጅጉ ተሸመድምዷል፡፡
3. የኢትዮጵያ ሲቢል ማኅበረሰብ ያለበት ሁኔታም ተመሳሳይ ነው፡፡ ከጊዜ ወደ ጊዜ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና የሙያና ሕዝባዊ ማኅበራት አመራር አባላት በተጠና ሁኔታ ለወያኔ ቅርበት ላላቸው የትግራይ ተወላጆች አሊያም በዘራቸው የትግራይ ተወላጆች በሆኑ ሰዎች እየተያዙ ነው፡፡ ከሁለቱም ያልሆኑ ኢትዮጵያዊያን የወያኔ ሎሌዎች እስካልሆኑ የመረዳጃ ማኅበር እንኳን ማቋቋምና መምራት እንዳይችሉ ተደርገዋል፡፡

ከላይ እንደተገፀው የተባበሩት መንግሥታት ባስቀመጠው ትርጓሜ መሠረት የዘር መድልዎ የሚፈፀመው ዘርን ወይም አስተሳሰብን መሠረት አድርጎ ሊሆን ይችላል፡፡ ዛሬ በአገራችን ሁለቱንም መሠረት ያደረገ የዘር መድልዎ እየተደረገ ነው፡፡ የዚህ መድልዎ ተጠቃሚዎች የትግራይ ዘውግ ማኅበረሰብና ለወያኔ ገዥዎች ስብእናቸውን የሸጡ ጥቂት የወያኔ አገልጋዮች ሲሆኑ ተጠቂው ግን በቁጥር እጅግ ብዙ የሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው፡፡

እንዴት ነው ይህንን አስከፊ የዘር መድልዎ መዋጋት ያለብን የሚለው ጥያቄ መሠረታዊና አንገብጋቢ ነው፡፡ ይህንን ጥያቄ ስንመልስ ፤

1. በረዥም ጊዜ ስሌት ከታየ ከዘር-መድልዎ ተጠቃሚ የለም - ሁሉም ተጎጂ ነው፡፡ ለጊዜው እየተጠቀሙ ያሉት ወገኖችም ከአጭር ወደ ረዥም የጊዜ ስሌት ሲሸጋገሩ አሁን እየጠቀማቸው ያለው ሥርዓት በረዥም ጊዜ አጥፊያቸው እንደሆነ ይረዱታል፡፡
2. በማናቸውም የዘርመድልዎ እንደታየው ሁሉ የመድልዎው ተጠቃሚ የሆነው ወገን አባላት በሙሉ ተጠቃሚ አይሆኑም፡፡ አብዛኛውን ጊዜ የተጠቃሚው ቡድን በአብላጫው አባላት ስም ይነገዳል እንጂ አብዛኛዎቹ ከፍርፋሪ የበለጠ ጥቅም አያገኙም፡፡
3. የዘር መድልዎን ለማጥፋት የሚደረግ ትግል አላስፈላጊ ወደ ሆኑ ጽንፎች እንዳይሄድና አሰቃቂ መዘዞች እንዳያስከትል ከመድልዎው ተጠቃሚ የሆኑ ወገኖች የአገዛዙን ኢፍትሃዊነትና ኢሰብአዊነት ተቃውመው በስማችን ይህ ግፍ ሲፈጸም ዝም ብለን አናይም ማለት ይገባቸዋል፡፡ የደቡብ አፍሪካን አፓርታይድ ለማስወገድ የስርአቱን ግፈኛነት ተቃውመው የታገሉ የነጭ ደቡብ አፍሪካውያን ሚና ምን ያህል ከፍተኛ እንደነበር ልብ ይሏል፡፡ እኛም ከትግራይ ተወላጆች ተመሳሳይ ነገር እንጠብቃለን፡፡ ምክንያቱም ግፍ የሚወልደውን አመፅ መቆጣጠር የማይቻልበት ሁኔታ ላይ ሊደረስ ይችላል፡ የሚል እምነት ስላለን።

በዚህ አጋጣሚ ዘረኛውን አገዛዝ ለመፋለም ቆርጠው ለተነሱ የትግራይ ተወላጆች እና የዘረኛው የመለስ ዜናዊ መሳሪያ በመሆን በወገናቸው ላይ ለደረሰው የዘር ውርደትና ዘረኛ ዘረፋ ተጠያቂ ነን በሚል ቁጭት ወያኔን አምረው ለመታገል ለተነሱት የብአዴን፣ የኦህዴድ፣ የደህዴንና የቀድሞ የኢህአዴግ አባላት ያለንን አክብሮት እንገልፃለን፤ ሌሎችም አርዓያነታቸው እንዲከተሉ እናበረታታለን፡፡

መለስ ዜናዊና ዘርፈው፣ ግፍ ሰርተውና ደም አፍሰው የመይጠግቡ ጓደኞቹ የገነቡት ዘረኛና አድሏዊ ሥርዓት በላያችው መፍረሱ አይቀርም፡፡ ስለዚህ ከእዚህ የግፍ ስርአት ጋር በዘር ይሁን በጥቅም የተሳሰሩ ወገኖቻችን የመለስ አደገኛ አካሄድ በሃገራችንና በሁላችንም ላይ እንዲያጣላ ያደረገው የጨለማ ደመና ያረገዘው የመከራ ዶፍ ለማሰቆም ቆርጠው ሊነሱ የሚገባበት ሰአት አሁን ነው፡፡ ይህንን ብካይ አምራች የሆነን ዘረኛ ሥርዓት አፈራርሰን ፍትህ የሰፈነባት፤ ልጆቻችን ተፋቅረው የሚኖሩባት ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ለመገንባት የምናደርገውን ትግል በዘር ስልጣን የተሰጣቸው የወያኔ ጀነራሎች የደህንነት መኮንኖች ሊገቱት አይችሉም፡፡ ትግሉ እየከረረ ሲመጣ መለስና በመለስ አገለጋይነታቸው የብዙ ሚሊዮኖች ዶላር ጌቶች የሆኑት ጀነራሎች በየፈረንጅ ሃገሩ ያስቀመጡትን ብር እያጣጣሙ ለማርጀት ባገኙት ቀዳዳ ሁሉ ሃገር ጥለው መሸሻቸው አይቀርም፡፡ የአምባገነኖች የጀግንነት ጉራ መጨረሻው ይህ እንደሆነ ከቅርቡ ታሪካችን አይተነዋልና፡፡ ህዝብ ግን በክፉም በበጎም አብሮ ከመኖር ሌላ አማራጭ የለውም፡፡ ይህን መረዳቱ ተረድቶም ለዘላቂው ማምለጫ ለሌለው የጋራ ህይወት ህዝብ በዘር ልጓም ሳይታሰርና የአምባገነኖችን የቅጥፈት ፕሮፓጋንዳ ከቁብ ሳይቆጥር በአንድነት ሊቆም ይገባዋል፡፡ ይህ የጋራና የአንድነት የትግል ጥሪ መለስ ዜናዊ የዘረኛና የዘረፋ ስርአቱ መከላከያ አድርጎ ከሌላው ወገኑ ጋር ሊያጋጨው የሚፈልገውን የትግራይ ወገናችንን ይመለከታል። ምኞታችን የእዚህን ታሪካዊ ጥሪ ክብደት በመረዳት የትግራይ ልሂቃንና ህዝብ አዎንታዊ ምለሹን ይሰጣሉ የሚል ነው፡፡

በግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ የህዝብ ግንኙነትና ቅስቀሳ ዘርፍ በሳምንት አንዴ የሚዘጋጅ ድርጅታዊ ልሳን

የፖስታሳጥን ቁጥር :- POBox: 4916
2003EX Haarlem, The Netherlands

# ሃይለ ሀሳብ

## የህብረት ትግል ለምን?

### ዶር ብርሃኑ ነጋ

ከሁለት ሳምንታት በፊት ዋሸንግተን ዲሲ ላይ ባደረግሁት ንግግር የኢትዮጵያችንን የወደፊት የፖለቲካ ዕጣ በሚመለከት አራት "የሊሆን ይችላል" ትንተናዎችን አቅርቤ፣ ተመራጩ "ሁለተኛው አማራጭ፣ አስቀድሞ በተዘጋጀና የሚሄድበትን በሚያውቅ የጋራ ትግል ለውጡ ቢመጣ የሚለው ነው" በሚል የግንቦት ሰባትን ርዕይ ለታዳሚው አካፍዬ ነበር ። ለዚህም የህብረት ትግል አስፈላጊነትን በተመለከተ አፊሴላዊ ጥሪ ከዲሲ መድረክ አድርጌ ነበር ። በዛሬው ውይይታችን፣ ይህ ዲሲ ላይ በጥሪ ደረጃ የተወረወረ ሃሳብ ለምን አስፈላጊ እንደሆነ፣ እስከዛሬስ ለምን ሳይሰምርልን እንደቀረ፣ ካለፉት የህብረት ተሞክሮዎቻችን ምን ልንማር እንደምንችል የሚጠቃቅሱ ጥቂት ጉንተላዎች አደርግና፣ ሃሳቡን በናንተም ተሳትፎ በጋራ እንድናዳብረው እፈልጋለሁ ። አሜሪካኖቹ "የታውን ሆል ሚቲንግ" በሚሉት መልክ "የሃገር ወዳዶች ሸንጎ" ተቀምጠን መመካከር ከቻልን ከምዕራባውያኑም በተሻለ፣ ከመሪዎች ዲስኩር ይልቅ፣ የህዝቡ ተስፋና ፍርሃት የሚደመጥበት መድረክ ሊሆን ስለሚችል ሃገራችን ትጠቀማለች ብዬ አስባለሁ ።

## *የህብረት የትግል መድረክ ለምን ያሻናል?*

ሃገራችን ኢትዮጵያ በልዩ ቀለማት ያሸበረቀች ነች ። በአስር ሺህ ጫማ ከፍታ ከሚኖሩ ደገኞች እስከ 11 ጫማ ከባህር ወለል በታች እስከሚኖሩ ቆለኞች፣ ከ80 በላይ ቋንቋዎችን የሚናገሩ ብሄረሰቦች፣ ሶስቱ የአለም ትላልቅ ሃይማኖቶች የሚገኙባት፣ አረብ ከሚመስሉ የወሎ ቆነጃጅት ሌላውን የአፍሪካ ክፍል የሚያስንቁ ሎጋ አኝዋኮች፣ በነዚህ ሁሉ የህዝቦች ህብር የተዋበች ሃገር ናት ። ከነዚህ የቀለም፣ የቁመና፣ የሃይማኖት፣ የቋንቋ ልዩነቶች የሚመነጩ የስነ ልቡና መለያየቶችም እንዳሉን መቀበል ሊያስፈራን አይገባም ። ደገኞቹ እህቶቻችንን ለቆለኞቹ አኝዋኮች ለመዳር ደገኞቹ ደስተኛ እስከንሆን ድረስም፣ ቀስ በቀስ እየቀረፍነው የምንሄደው ረጅም ጉዞ ይመስለኛል ። የደገኛውም ብቻ ሳይሆን፣ ያቺ ውበቷን ፍንትው ለማድረግ በከንፈሯ ላይ የሸክላ ገል የምታጠልቅ የሃመር ቆንጆ፣ በቀይ ዳማው ጎንደሬ ገፅ ላይ መልከ መልካምነትን እስኪታይ ድረስም አብሮን ያዘግም ይመስለኛል ። ስለሆነም፣ የመጀመሪያው ስምምነታችን ሊሆን የሚገባው፣ ኢትዮጵያ የአንድ ህዝብ ሃገር ናት ስንል፣ በቋንቋም በስነ ልቦናም፣ በዘውግም የተለነቆጠች ወይም ታሽታ አንድ የሆነች ሃገር ናት ማለታችን ሳይሆን፣ ይህ ከላይ ያነሳናቸው ተፈጥሮአዊ ልዩነቶች እንዳሉም ሆነው፣ እነዚህን ተፈጥሮአዊ ልዩነቶች አልፎ ከበስተወዲያ የዘገንነው፣ በሰብአዊ ክህሎታችን አምጠን የወለድነው አንድነት አለን ማለታችን ብቻ ነው ። ይህም አንድነት ከነፃነት ጥማታችን የተወለደ፣ ከዜጋዊ ግዴታችን በውዴታችን ያመጣነው፣ እንደ ህዝብ በጋራ አናስደፍርም ያልነው፣ የሞትንለት የተሰየፍንለት ብርቅዬ ነው ። ገብርዬ፣ ባልቻ፣ ሃይለማርያም ማሞ፣ ገረሱ ዱኪና ሌሎችም አርበኞቻችን፣ እምቢ ለእንግሊዝ፣ እምቢ ለጣሊያን፣ እምቢ ለፋሽስት ብለው፣ ደረታቸውን ለወራሪዎች ሰጥተው፣ ለሃገራቸው ጋሻ ሲሆኑ፣ ስለልዩነታቸው እያሰላሰሉ ሳይሆን፣ ሃገራቸው በእቅፏ ለያዘቻቸው ዜጎቿ ሁሉ ጠለላ እንድትሆን፣ ለነፃነቷ ያደረጉት መስዋእትነት ነው ።

ተፈጥሮአዊ ልዩነቶች አሉን፣ ቢሆንም፣ በላቀና ለነፃነት በተከፈለ መስዋእትነት የተፈተለ፣ የተጋመደና የተሸረበ፣ የአንድነት ታሪክ ባለፀጋዎችም ጭምር ነን ። ስለሆነም፣ ስለ ህብረት ትግል ስናሰላስል፣ የዛሬውን የቋንቋና የስነ ልቡና ልዩነቶች መኖር፣ እንደ ጋሬጣ ሳይሆን፣ የዚህችን ታሪካዊት ሃገር ቀጣይነት እንደሚያጠብቅ የማሪያም መቀነት ልናየው ይገባል እላለሁ ። የህብረት ትግል አንዱ ዋነኛ ምክንያት ይህ ልዩነትና አንድነት የሚያስገድደው የፖለቲካ ዘይቤ ይመስለኛል ። ቅድም አያቶቻችን እንደ ምእራባውያን በጭካኔ በእሳትና ብረት እየቀጠቀጡ ያዋደዱት ሳይሆን፣ ለሃገራዊ አንድነት በጋራ ባፈሰሱት የነፃነት ደምና በጋራ ድህነትና ደዌ ባለቀሱት እንባና ሰቆቃ ተቦክቶ የተለሰነ ሃገራዊ አንድነት በመሆኑ፣ በስሱነት ልንይዘውና ልንንከባከበው ያሻል እላለሁ ።

ኤድዋርድ ጊበን እንዳለው አለሙን ረስተነው በአለሙም ተረስተን ለዘመናት ከባጀን በሁዋላ፣ ድንገት ብንን ስንል፣ እጅግ ብዙ ርቀው ስለጠበቁን፣ ከአውሮፓውያኑ ለመድረስ "ፈጣኑ መንገድ እኔ የያዝኩት ብቻ ነው" በሚል፣ ሁላችንም ጉጉታችንና ረሃባቸን ባስገደደን መንገድ መጓዝን ስለመረጥን፣ ብዙ የአቋራጭ መንገዶቸን ስናሰላስልና ስንሯሯጥ፣ ጊዜ አግኝተን ለመደማመጥ ባለመቻላቸን፣ ዛሬ ከ99 የማያንሱ ፓርቲዎቸ ቀፍቅፈን እንገኛለን። በአለሙ የታዩ የፖለቲካ ዝንባሌዎች ሁሉ ማራጋፊያ የሆንን ይመስል፣ ከህገ መንግስታዊ ዘውደኛ እስከ ወያኔያዊ ሃገር አውዳሚ ሃይል ድረስ፣ በየመስኩ የተሰለፈው ኢትዮጵያዊ የትዬለሌ ነው ። አንድ ጓደኛዬ ሲቀልድ ከምንለብሳቸው ሳልቫጅ ልብሶች ጋር አብረው የሚመጡት የቀድሞ ባለቤቶቻቸው ቆሌዎች እየሰፈሩብን፣ ከአውሮፓ እስከ አውስትራሊያ ከኢንዶኔዥያ እስከ ደቡብ አሜሪካ ያንቀዥቅዡናል እያለ ያሾፋል ። በትምህርት ስርአታችንም፣ ከአሜሪካ የሰላም ጓዶች እስከ ህንድ መምህራን የተቀየጥን፣ በከፍተኛ ትምህርት ተልእኳችንም፣ ከምእራብ ጀርመን እስከ ኪዩባ ህዝባዊ አብዮት እጅግ በተለያዩ ባህሎችና ርእዮተአለሞች የተጠመቀ የተማረ ሃይል ያፈራች ሃገር በመሆኗና፣ እንደ ጃፓናውያን አንድ በሚያደርገን ሃገራዊ ትውፊትና ልማድ የታሰረ ምሁር ባለመሆኑ፣ ኢትዮጵያንም የምናይበት አይን እንደ ስልጠናችን ዝብርቅርቁ የወጣ ነው ማለት ማጋነን አይመስለኝም ። እንዲህ የተቀየጠ ምሁራዊ ሃይል፣ በተለይ በመጀመሪያው ዴሞክራሲያዊ ርምጃ (መድረክ) ወቅት፣ ተፅእኖው ከፍተኛ ስለሆነ፣ ሁሉም የአቅሙን ወርውሮና ተንፍሶ እፎይ የሚልበት የጋራ መድረክ ካልተመሰረተ፣ ችግራችን በጥቂት ድርጅቶች ወይም መሪዎች "አውቅልሃለሁ" ባይነት ሊፈታ የሚችል ነው ብሎ አቃልሎ ማየት ግብዝነት ይመስለኛል። ይህ ሌላው የህብረት ትግልን የግድ የሚያደርገው ምክንያት ይመስለኛል ።

የምሁራዊው ሃይሉ እንደ ስልጠናውና እንደ ርእዮተአለሙ ዝብርቅርቅ ከመሆኑ ባሻገርም፣ ባለፉት አራት አሰርተ አመታት፣ አገዛዝን በመቃወም በተደረጉት ትግሎች የተሳተፈው ሃይል እጅግ ብዙ ሆኖ ሳለ፣ በተሰለፈባቸው ድርጅቶችና ርእዮቶች ሸንፈት ሲገጥመው፣ በአለሙ ለመበተን ተገዶ አዲስ "የዳያስፖራ" ማህበረሰብ በመመስረቱና፣ ከአዲስነቱም በመነጨ ከታደጉት ሃገሮችና ህዝቦች ቋንቋና ባህል ጋር እስኪላመድ ድረስ አድካሚና ግር የሚልም ስለሆነበት፣ ይህ የትግል ልምድ ያለው ሃይል የግል ኑሮውን ለማሸነፍ እጅግ ተበታትኖ ይታያል ። እንደ ኮሪያዊያኑ፣ እንደ ቻይናውያኑ ጠንካራ ማህበረሰቦችን ገና አልመሰረተም ። ከዚህ መበታተኑም በመነጨ በሃገሩ ለሚደረጉት የፖለቲካ ትግሎች፣ አስተማማኝ ደንደስ ሊሆን አልቻለም ። በዚህ ላይ የሚሰጠው ውሱን ድጋፍም በብዙ ትናንሽ ድርጅቶች ዙሪያ የተከፋፈለ በመሆኑ፣ አመርቂ ድጋፍ ማድረግም አልተቻለውም። የፖለቲካ ትግሉ መተባበር፣ ይህን የተባበተነ ትግል በማሰባሰብ፣ ትልቅ የአቅም ግንባታ ለማድረግ ያስችለዋል ብዬ አስባለሁ ።

በሶስተኛ ደረጃ፣ ወያኔ አጀንዳው ያደረገው የብሄረሰቦች ጉዳይ፣ የወያኔ የግል ጉዳይ ይመስል የተተወ በመሆኑና፣ አልፎ አልፎም የብሄረሰቦችን መብት ያነሳ ሁሉ እንደ ፀረ አንድነት እየታየ የተወገዘባቸው ሁኔታዎች፣ (በተለይ በዳያስፖራው ማህበረሰብ ጫሂ መገናኛ ብዙሃን) ብዙ ስለነበሩ፣ ወያኔ በዘውግ ለመከፋፈልና እድሜውንም ለማራዘም እንዲችል በር ተከፍቶለታል ። ኦነግን እየመነጠርኩ ነው በሚል ሽፋን በኦሮሞው ህዝብ ላይ እልቂትን ያወርድ የነበረው ወያኔ፣ ቀስ ብሎ የኦጋዴን አርነት ግንባርን በመዋጋት ስም በኢትዮጵያውያን ሱማሌ ወገኖቻችን ላይ ግፍና አበሳን ሲያወርድ ከርሞ ነበር ። አሁን ደግሞ፣ የመንግስት ግልበጣ ሙከራ ተደረገብኝ በሚል ከለላ፣ የብሄረ አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ አባላትን እመነጥራለሁ በሚል ቀቢፀ ተስፋ፣ በአማራው ህዝብ ላይ ከፍተኛ ብካይ በማድረስ ላይ ይገኛል ። ነገ ደግሞ "አረና ትግራይን" የአማራ ቡችሎች ብሎ፣ በመቀሌ ሃውዜንና አዲግራት የአፈና ርምጃ ቢጀምር ከቶ ሊገርመን አይችልም ። ከነዚህ ሁሉ የወያኔ በትሮች የተማርነው ነገር ቢኖር ግን፣ ወያኔ በስልጣኑ እስከመጡበት ድረስ ለማንም የማይመለስ መሆኑንና፣ በተናጠል በየተራ ከምንመተር፣ የጋራ ጉልበታችንን አስተባብረን የጋራ ጠላታችንን መመከት አማራጭ የሌለው መሆኑን፣ የ18 አመታት እንግልታችን ሁላችንንም ያስተማረበት ወቅት ላይ መድረሳችን ነው ።

የህብረት ትግልን አስፈላጊነት ብዙዎቹ ድርጅቶችና አመራሮቻቸው የተረዱበት ወቅት ላይ ደርሰናል የሚል እምነት አለን ። ስለሆነም የብሄረሰቦች ጉዳይ ለወያኔ የስልጣን ገበጣ መጫወቻ የሚተው ሳይሆን፣ አጀንዳውን ከወያኔ ቀምተን፣ አላማችን አድርገን የተነሳነው የዜጎች ነፃነት ታላቅ ህልም፣ የወል ጥያቄ የሚያነሱ ዜጎችን መብት ሳያስከብር፣ ካለመበት መድረስ እንዳይቻለው አውቀን፣ በየዋህነት ወደጎን ገሸሽ የተደረገውን የብሄረሰቦች ጉዳይ የሚመለከተን መሆኑን አስምረንበት፣ ከኦነግ የተለያዩ ሃይሎችም ጋር ሆነ፣ በወያኔ አፍንጫ ስር "ወጊድ ለወያኔ ዘረኝነት" ብለው የሚረባረቡ ሌሎች ሀይሎቸን አጋርነታቸንን በማሳየት ብርቱ ልንላቸው ይገባል ።

በአራተኛ ደረጃ፣ ግንቦት ሰባት ይዞት የተነሳው ውሱን አላማ፣ ይሄውም የሃገሪቷን አንድነት አስጠብቆ ከዴሞክራሲያዊ የስልጣን ሽግግር የምትደርስበትን ሁኔታ ማመቻቸት ግብ፣ ሁሉንም የፖለቲካ ሃይሎች ያካተተን የሽግግር መድረክ ያለመ በመሆኑ፣ ወደዚያም መድረሻው ድልድዩ ሃገራዊ አንድነትንና ዴሞክራሲን የሚሹ ሃይሎችን ሁሉ በጋራ ያስተባበረ ትግልን በማጧጧፍ በመሆኑ፣ ከግባችን ለመድረስ ከህብረት ትግል ውጪ የሚቻል አይደለም ። በነዚህ ሁሉ ምክንያቶች የህብረት ትግል እጅግ ተመራጭ ነው ። ግን እስከዛሬ ለምን መተባበር ሳይቻለን ቀረ?

## *የህብረት ትግል ሙከራዎች ያገጠሙት እክሎች ምን ነበሩ?*

ይህን ርዕስ ሙከራዎቹን ያደረጉት ድርጅቶችና መሪዎቻቸው ቢናገሩት የሚቀልም ሆነ ይበልጥ ተገቢ ይመስለኛል ። ከራሱ ከኢህአዴግ ጀምሮ ብዙ የህብረት ትግል ሙከራዎች ተደርገዋል ። በደርጉ ዘመንም ኢጭአት፣ ኢማሌድህ ወዘተ የተሰኙ የገዢው ሃይል የህብረት ሙከራዎች እንደነበሩ አይዘነጋም ። ኢማሌድህ በድርጅቶች ህብረት ተጀምሮ፣ በሂደት አንድ የኮሙኒስት ፓርቲ እንመሰርታለን ተብሎ፣ በመጨረሻ ገኖ የወጣው የመንግስቱ ሃይለማርያም ወታደራዊ ቡድን፣ ሰደድ፣ "በቆራጡ መሪያችን ዙሪያ ካልሆነ፣ በድርጅቶች ህብረት ፓርቲ መመስረት አይቻልም" ወደሚል ጅልነት ተሸጋገረ ።

ደርጉ ወታደራዊ ጡንቹ ፈርጥሞ ኢዲዩንም ኢህአፓንም ካዳከማቸው በሁዋላ፣ የዛሬ 25 አመታት ገደማ፣ ከአንፃራዊ የሃይል ደካማነታቸው በመነሳት፣ ሃይላቸውን ለማስተባበር በማሰብ፣ ኢዲዩና ኢህአፓ በሊበራል አስተሳሰብ ዙሪያ የተስማማ የጋራ ግንባር አውጀው ነበር ። ሆኖም በመርህ ላይ የተመሰረተ ሳይሆን ደካማ ጉልበትን ለማሰባሰብ የተደረገ ሙከራ ስለነበር፣ ከዛሬ 18 አመታት በፊት ወያኔ አዲስ አበባ ሲገባ፣ ህብረቱ ሊፈርስ ችሏል ።

**ይቀጥላል**

## የወያኔ የፍርድ ቤት ድራማ በእነ ብርጋዲየር ጄኔራል ተፍራ

ከገጽ 1 የዞረ

በተያያዘ ዜናም ህብረተሰቡ የሀሰት ምስክሮችን በመለየት ምስክሮቹ ከዚህ ወራዳና የኢትዮጵያውያን ባህሪ መገላጫ ካልሆነ ተግባር እንዲቆጠቡ ማድረግ እንደሚገባው አስተያየት ሰጪዎች ተናግረዋል። በአዲስ አበባ የግንቦት 7 አባል የሆኑ ግለሰብ በሰጡት የግል አስተያየት፣ እርሳቸውም ሆኑ ሌሎች ኢትዮጵያውያን እንዲህ አይነቱን ታሪክንና ባህልን የማጉደፍ ድርጊት ለማስቆም እየተንቀሳቀሱ መሆናቸውን ገልጸው፣ እርሳቸውም የምስክሮችን እውነተኛ አድራሻ፣ ስምና ማንነት ለይተው በበመዝገብ ላይ መሆናቸውን ተናግረዋል። ህብረተሰቡ የሀሰት ምስክሮችን የመኖሪያ አድረሻ፣ ማንነትና ባህሪ ባካባቢው ላሉ የግንቦት ሰባት አባሎች እንዲያሳውቅ ወይም በግንቦት 7 አድረሻ እንዲልክ ጥሪ ያቀረቡ ሲሆን፣ ምስክሮችም በተራቸው በሰጡት የሀሰት ቃል የሚጠየቁበት ቀን እሩቅ እንደማይሆን ተናግረዋል።

ግንቦት 7 ኢትዮጵአን በአጭር ጊዜ ውስጥ ነጻ ለማውጣት ከፍተኛ ዝግጅት በማድረግ ላይ ሲሆን፣ በወያኔው ጥቅማጥቅም በመደለል ወያኔን በማገልገል ላይ ያሉ ሁሉ ፈጥነው እርምጃ መውሰድ እንዳለባቸው አሳስቧል።

## ታዋቂ ኢትዮጵያውያን አገር ጥለው በመውጣት ከገጽ 1 የዞረ

ወያኔ በሰበብ አስባቡ ለስልጣኑ አደገኛ መስለው የታዩትን ታዋቂ ሰዎች ሁሉ በማሳደድ አገሪቱን ሰው አልባ ለማድረግ ቆርጦ መነሳቱን የሚናገሩት አስተያየት ሰጪዎች፣ ባለፈው ወር ሌላው ታዋቂ ኢትዮጵያዊ የሆኑት አቶ ተካልኝ ገዳሙ የአቢሲኒያ ባንክ ፕሬዚዳንት ሆነው በማገልገል ላይ በነበሩበት ጊዜ በቀረበባቸው የሀሰት ክስ አገር ጥለው መሰደዳቸውን ለዋቢነት ጠቅሰዋል።

የወያኔውን ዘረኛ አገዛዝ በኢትዮጵያውያን ላይ የሚያደርሰውን ግፍ በአስቸኳይ ለማስቆም የሚቻለው ሁሉም ተባብሮ አገዛዛዙን ከስልጣን ላይ ማውረድ ሲቻል ብቻ መሆኑን የሚናገሩት አስተያየት ሰጪዎች፣ ወያኔ በስልጣን ላይ እስካለ ድረስ ሁሉም ታዋቂ የአገሪቱ ዜጎች ቀስ በቀስ ለመሰድድ እንደሚገደዱ አክለው ተናግረዋል።

ጠበቃ አበበ ወርቄ በሽምግልና እድሚያቸው ለአገራቸው ባደረጉት ከፍተኛ አስተዋጾ መሸለም ሲገባቸው በሀሰት ክስ አገር ጥለው እንዲሰደዱ መገደዳቸው ብዙ ኢትዮጵያውያንን ማበሳጨቱ ታውቋል። አቶ አበበ የተከሰሱበት አዲስ ብሮድካስቲንግ ኩባንያ የግንቦት ሰባት መስራችና ሊ/ር የሆኑት ዶር ብርሀኑ ነጋ ከሌሎች ባለሀብቶችና ምሁራን ጋር በጋራ የመሰረቱት ኩባንያ መሆኑ የታወቃል።

ወያኔ በኩባንያው ላይ የከፈተው ዘመቻ ዶ/ር ብርሀኑን ለመበቀል ወይም የግንቦት ሰባትን ሀይል እየፈራ በመምጣቱ ምክንያት ሊሆን እንደሚችል ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማሪያም ለአሜሪካ ድምጽ መናገራቸው ይታወሳል።

## መለስ ስልጣን መልቀቅ የለበትም የሚል ዘመቻ ሊጀመር ነው

ከገጽ 1 የዞረ

መለስ ይህን የሚለው በየግምገማው "ተቸካይ፤ ከጊዜው ጋር ራሳቸውን የማያሳድጉ" የሚላቸውን አብዛኞቹን ነባር ባለስልጣኖችና የድሮ አጋሮቹን በዘዴ ሊያስወግዳቸው ስለፈለገ ብቻ ነው" ሲሉ የሰውየውን የሁዋላ መሰሪ ታሪክ ዋቢ በማድረግ በዝርዝር ያስረዱት እነኚሁ የቅርብ ሰዎች፤በተቀናበረ መንገድ እነሱን በፎርፌ ካስበላ በሁዋላ እርሱ እንደ ልምዱ " ይህች ናት ጨዋታ" ን እያዜመ በሜዳው ላይ መጋለቡን ይቀጥላል ብለዋል።

መረጃውን ያደረሱን ወገኖች -በጉዳዩ ዙሪያ አንጋፋው የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም ሰሞኑን የሰጡት ሀሳብ በተወሰነ ደረጃ ውስጥ ለውስጥ እየተደረገ ያለውን ለመግለጥ የሞከረ ነው ባይ ናቸው።

በጉዳዩ ላይ ምን ይላሉ? ተብለው በጋዜጠኛ የተጠየቁት ፕሮፌሰር መስፍን፤"መለስ መቼ ነው እለቃለሁ ያለው?" በማለት ነበር ጥያቄውን በጥያቄ የመለሱት። አያይዘውም:- "የለቀቁኝ እንደሆነ ነው የሚለው ፤ይህ ደግሞ አዲስ ነገር አይደለም ፤ ያኔም፤አሁንም በራሱ ላይ በባለቤትነት እየወሰነ አይደለም፤ አደናጋሪ እና በቅድመ ሁኔታ የታጠረ ነገር ነው እየተናገረ ያለው" ብለዋል፡፡

በጅማ፤ በሀዋሳ፤ በናዝሬትና በባህርዳር የሚገኙት የግንቦት 7 ዘጋቢዎች ያሳባሰቧቸው የህዝብ አስተያዬቶች እንደሚያመላክቱት ደግሞ፤ብዙዎቹ የየከተሞቹ ነዋሪዎች መለስን እንደ መሪያቸው ፤ በጉልበቱ እየተንፈራገጠ ያለውን የህወሀት ገዥ ቡድንም እንደ ህጋዊ መንግስት ስለማይቆጥሩት፤"የሱ ወጣ ወረደ መባል- አይሞቃቸውም፤አይበርዳቸውም። ምክንያት- በነሱ ልብ ውስጥ ከወረደ ብቻ ሳይሆን ከተቀበረ ቆይቷልና።

"የህዝብን ድምፅ በጠራራ ፀሀይ ዘርፎና በህዝበ-ውሳኔ ላይ መፈንቅለ -መንግስት ፈፅሞ በጠመንጃ ህገ-ወጥ አርካብ ላይ የተቀመጠ ወንጀለኛ -በፈቃዱ ስልጣን በመልቀቅ የመጀመሪያ ኢትዮጵያዊ መሪ እሆናለሁ ማለቱ ነው ያሳቀን" ያሉት የየከተሞቹ ነዋሪዎች፤"በገዛ ፈቃድ ስልጣን የመልቀቅ ታሪክን ለማፃፍ ቢያንስ የ 1997ቱ ምርጫ የሰጠውን እድል መጠቀም በመጠኑም ቢሆን ማስተሰርያ ይኖረው ነበር"ብለዋል።

"አሁንማ..."ይላሉ ነዋሪዎቹ ትን የሚል ጥቁር ትዝታ እየገለመማቸው"....አሁንማ ምን ያደርጋል?ከተባለው በላይ ተሂዶ አይደለም መለስ ኢህአዴግ ሙሉ በሙሉ እንኳ ቢለቅ ፤የታሪክ ማቅለሚያ ብእሩ ላይጠገን ተሰብሯል።የታሪክ ባቡሩ ላይመለስ ቦታውን ለቅቆ ተንቀሳቅሷል" ብለዋል።

በመሆኑም የተባለው እንኳ እውነት ሆኖ መለስ ስልጣን ቢለቅ -የዚህ ዓይነቱን በአገሪቷ የአጣብቂኝ ጉዞ አንድምታ ላይ ምንም ለውጥ የማያመጣ የስልጣን ሽግሽግ እንደ "ዲሞክራሲ" ምልክት ተደርጎ ጡሩምባ መነፋቱ ገርሞናል የሚሉት ነዋሪዎቹ፤ "በብጫቂ ዶሴ የታጨቀውን ና መቼም ቢሆን ሊዘነጋ የማይችለውን ፀያፍ ታሪክ ተሸክሞ ፤" መሄዴ ነውና ሸኙኝ ካለ፤ እርሱ ራሱ እንደሚለው መንገዱን ጨርቅ ያርግለት"ብለዋል።

ሆኖም፤ እንደ ኢትዮጵያውያኑ አባባል፤መለስ ወረደም ተደበቀ በኢትዮጵያ ህዝብ ፊት ለፍርድ መቅረቡ ሳይታለም የተረጋገጠ ሀቅ ነው።

## ወያኔ እድሜውን ለማራዘም ሆን ብሎ የሃይማኖት ግጭቶች

ከገጽ 1 የዞረ

በማክሰኞው ግጭት ሶስት ሰዎች በወያኔ ቅልብ ፖሊሶች ሲገደሉ በርካቶች ደግሞ ቆስለዋል። አንድ እርጉዝ ሴትም ክፉኛ መደብደቡዋንና ባሏም በድብደባ ብዛት በደረሰበት ጉዳት ሆስፒታል መተኛቱ ታውቋል።

ወያኔ በአገሪቱ ውስጥ ምንም አይነት የተቃውሞ ሰልፍ እንዳይደረግ መከልከሉ አገዛዙ የህዝቡን ሀይል ከጊዜ ወደ ጊዜ እየፈራ መምጣቱን እንደሚያሳይ የሚናገሩት ምንጮቻችን፣ የደሴና የአካባቢው ህዝብ የወያኔን እገዳ በመጣስ ያደረገው ተቃውሞ በሌሎችም ህዝቦች መደገም እንዳለበት የሚናገሩ በርካቶች ናቸው።

ወያኔ ክርስቲያንና ሙስሊም ወንድሞችና እህቶች በብዛት በሚገኙባቸው ከተሞች በሀይማኖት ሰብብ ግጭቶች እንዲነሱ የሚያደርግ ሲሆን፣ የተለያዩ ብሄሮች በሚገኙባቸው አካባቢዎች ደግሞ በዘር ሰበብ ግጭቶችን በማስነሳት ህዝብ ከህዝብ እንዲተላለቅ እንደሚያደርግ ታዛቢዎች ይናገራሉ።

በደሴ የሚኖሩ ሙስሊሞች "የአርሴማ ቤተክርስቲያን እንዳትሰራ ተቃውሞ አቅርበዋል" በሚል የሀሰት መልስ ፣ ሙስሊምና ክርስቲያኖችን ለማጣለት ወያኔ አቅዶ የነበር ቢሆንም፣ ሙስሊም ወንድሞች ግን እኛ " ቤተክርስቲያን አትስሩ አላልንም፣ ክስም አላቀረብንም" የሚል መልስ ለክርስቲያን ወንድሞቻቸው በመስጠታቸው የወያኔ ድብቅ ተንኮል ሊጋለጥ ችሏል። ሙስሊሞቹ በአዲስ አባባ የራጉኤል ቤተክርስቲያንንና ና የአንዋር መስጊድን በምሳሌነት በማንሳት ተቃውሞ አለማቅረባቸውን የገለጹ ሲሆን፣ በአርሴማ ቤተክርስቲያንና ባቅራቢያው ባለው መስጊድ መካከልም የ4 ኪሎ ሜትር እርቀት እንዳለ ታውቋል።

የዘረኛው መለስ ዜናዊ ተላላኪና ደንገጡር በረከት ስምኦን ፣ ግጭቱን ያስነሱት ከጀርባ የፖለቲካ አጀንዳ ያላቸው ናቸው የሚል መግለጫ መስጠቱ ትክልል ናቸው ያሉት አንድ የደሴ ነዋሪ፣ ከጀርባው አሉ የተባሉት የፖለቲካ ሀይሎች ግን ሌሎች ሳይሆኑ ራሳቸው ወያኔዎች ናቸው ብለዋል።

የደሴ ከተማ በወያኔ ቅልብ ፖሊሶች ቁጥጥር ስር የዋለች ሲሆን፣ ያገዛዙ ባለስልጣናትም ህዝቡን ለማስፈራራት በማሰብ "ጉዳዩ የፖለቲካ አጀንዳ ስላለው ወደ ቤተክርስቲያኒቱ ክልል እንዳትሄዱ" እያሉ በመኪና በመዘር ሲቀሰቅሱ መዋላቸውን ምንጮች ተናግረዋል።

የህዝብን ሀይል በጠመንጃ ማፈን አይቻልም የሚሉት አንድ የግንቦት ሰባት አመራር፣ አገዛዙ ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚደርስበትን ተቃውሞ በጠመንጃ ለማፈንም እንኳ እየተቸገረ የመጣው ህዝቡ ወደ ሁዋላ ሊመለስ በማይችልበት የመጨረሻ ደረጃ ላይ በመገኘቱ ነው ብለዋል።

በረዥም ጊዜ ስሌት ከታየ ከዘር-መድልዎ ተጠቃሚ የለም - ሁሉም ተጎጂ ነው፡፡ ለጊዜው እየተጠቀሙ ያሉት ወገኖችም ከአጭር ወደ ረዥም የጊዜ ስሌት ሲሸጋገሩ አሁን እየጠቀማቸው ያለው ሥርዓት በረዥም ጊዜ አጥፊያቸው እንደሆነ ይረዱታል፡፡ በማናቸውም የዘርመድልዎ እንደታየው ሁሉ የመድልዎው ተጠቃሚ የሆነው ወገን አባላት በሙሉ ተጠቃሚ አይሆኑም፡፡ አብዛኛውን ጊዜ የተጠቃሚው ቡድን በአብላጫው አባላት ስም ይነገዳል እንጂ አብዛኛዎቹ ከፍርፋሪ የበለጠ ጥቅም አያገኙም፡፡

ርዕሰ አንቀጽ


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**

**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

በ17870 KHZ በ 16 ሜትር ባንድ እና በ18350 KHZ በ19 ሜትር ባንድ ላይ የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።



**ውድ አንባቢዎቻችን**

**ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ዎይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን።** g7radio@ginbot7.org